


# መድሃኒት ማግኘት

Espen Stranger-Johannessen
Sara Rumen Krotev
Loza Tadesse Mamo
2
አማርኛ am



ቶም የጥርስ ሕመም አለበት። ጥርሱ በጣም ያመዋል።



የጥርስ ሐኪም ማየት ያስፈልገዋል። ነገር ግን በመጀመሪያ ለሥቃዩ አንድ ነገር ያስፈልገዋል።



በአቅራቢያው ወደሚገኝ ፋርማሲ ነዳ።



“የጥርስ ሕመም አለብኝ” አለ። “ለዚህ የሚሆን ነገር አለህ?”



“አዎ፣ እዚህ አንዳንድ የህመም ማስታገሻዎች አሉ። ለእነዚህ ማዘዣ አያስፈልግም።”




“አመሰግናለሁ! ስንት ነው ዋጋው?”




“ዋጋው ዘጠኝ ዩሮ ነው። ነገር ግን የጥርስ ሐኪም ማየት አለብዎት።”



“እሺ! ነገ ጠዋት የጥርስ ሀኪሜን እደውልለታለው።”



“ጠንካራ መድሃኒት ከፈለጉ ከጥርስ ሀኪምዎ ወይም ከዶክተርዎ ማዘዣ ማግኘት ያስፈልግዎታል።”



“አመሰግናለሁ! ደህና ሁኑ።”

# LIDA Stories

lidastories.net

## መድሃኒት ማግኘት


Espen Stranger-Johannessen
Sara Rumen Krotev
Loza Tadesse Mamo


CC BY